# ስም የስራ ልጅ ነው!

የተወራው ሁሉ ፣ እኩይ ፖለቲካ
የሚነቀል እና ደግሞም የሚሰካ
ያልበሰለ አእምሮ ፣ ሲያገኝ ብቻ እንጅ
ታሪክን ለሚያውቀው አይደለም የሚፋጅ!?
ዛሬ ነፍስ የዘራው ፣ የትብብር ዘሩ
ሎጬቤ ሳይረግጡለት ፣ ቢደሰቱት ጥሩ ፤
ግን ታሪክ አክባሪው ፣ ይህ አዲሱ ትውልድ
ለነገ ሲያዛጋ ፣ የ "እሳ!"ን ነጎድጓድ
ትችትን ቢያበዛ ፣ ወቀሳንም ቢያወርድ…
የእንጣላ ሙገት ፣ የይቅርታ 'ምጽዋት
"በአንድነት ቁስል ላይ ፣ ይኗል መሳግ እንጨት።"
የትላንቱ ትላንት ፣ ትላንትና አለፈ
የዛሬው ግን ዛሬ ፣ ዛሬኑ ለፈፈ
በቃ አሁን ተስማሙ ፣ "አባ" እና "ገዳ"
የሎሬት ጸጋየም ፣ መንፈሱ ረዳ።
ኩሽም አልን ካም ፣ ሴሜቲክም ሴም
'በሃሳብ ቢለያዩ ፣ የአባት ልጆች ወንድም።
ልዩነት ሁሌ አለ ፣ አፍ ታሪክ ይስታል
ይህ ትውልድም ሰንፎ ፣ ብዙ እድሎች ገድፎ ፤
"ድንጋይ ሰባሪ ቅል" አለ ታሪክ  አቅፎ።
ዛሬ ይህን ትቶ ፣ የበቀል ድሪቶ
በልዩነቱ እና በአንድነት ተግባብቶ
"ተቀበሉኝ" ላለ "ትብብር"  መስርቶ ፤…
ይህችንም ታሪክ ፣ አንዷትን ቁርጥራጭ
የስቃይን ውልደት ፣ የችግር ፍልጥላጭ ፣…
ባንቀባበላት ብንሞጋገታት ፣
በብእር አርጩሜ አጉል ብንነርታት
ለራበው ሰው ማልበስ ፣ ነው የጽድቅ ሃጢያት።
ለመወቃቀሱ ፣ ለመተቻቸት
ብዙ ግሮች አሉት ፣ የሁሉም ዜግነት፤
በዳይ ከተበዳይ
ቆራጥም ከአድር ባይ
ለመነካከስም ወይ ለመወቃቀስ
እስኪ ያ ህዝባችን ፣ ያቁም ደምን ማልቀስ።
ደምን አስለቃሹ ፣ የደምም ባለ አባት
እድሜው የሚረዝም ፣ የንግሰ-ህውሃት
የእኛወች ካብ ለካብ ፣ አይደል መተያየት?!
የእማማን ስሟን ምንም ባያካትት
መቸ ተወቀሰ ህዝባዊው ቅንጅት?!... *(CUDP)*
ቴወድሮስ የዘራው የአንድነቱ መህር
ከእሸቱ ሳይበላ ፣ ቢሰዋም በጅምር ፣

አ.ቢ.ሲ.ኒ.ያ ስታብብ በስራ
አይደለም ምኒሊክ ፣ ኢትዮጵያን ያስጠራ?!
ደሞስ “ትብብሩ” ፣ ሲያውጅ ስለአንድነት
ዘጠኝ ተጠቅሟል ፣ ቃለ-ኢትዮጵያዊነት።
        ግዴለም ይቆየን የትላንቱ ትላንት
        ዛሬ ላይ ቁጭ ብለን ነገን እናስባት።
        ይቆየን ቃላቱ ፣ ቅርጸ-ጽህፈቱ
        ማንም አይነካውም ከቅብረ-እትብቱ።
በስራ ብቻ እንጅ የአለም እምርታ
በክስ በሙግት ፣ ማን ማነን ረታ?!፣
ከስራም የሚጥም ፣ ልክ እንደ አድዋ
ሁሉም በአንድነት ፣ ለአንድ ከተሰዋ።
የዛሬም አንድነት ለነጻነት ‘እንጅ
ማንም አይቀብረው ፣ ስምን የስራ ልጅ።

በከፍያለው ፈንቴ

[የማከብራቸው ፣ አቶ ቴወድሮስ አበበ ፣ “ይድረስ ለነጻ አውጭው ወንድሜ” በሚል ለጻፉት ግጥም የተሰጠ መልስ።]()